# ታሪክ ሳያውቁ የታሪክ ሊቅ ሊሆኑ የዳዳቸው ዲስኩረኞች በለንደን እና በምሕራቡ አለም

ከእውነት መዝገቡ

ይህ ጽሑፌ የሚዳስሰው በለንደን ሃውስ ኦፍ ኮመን ፓሪትኩሊስ አዳራሽ (House of common, Portcullis house) ፤ በአውሮፓ የተለያዩ ከተሞች ፤ በምድረ አሜሪካ እንዲሁም እራሳቸው ለራሳቸው በዉሸትና በምእናብ ተንሳፈው በየድህረ ገጹ በሚሰልቁአቸው ጽሁፎቻቸው እና እንደለመዱት በየአውራ ጎዳናው ፋይዳ የሌለው  ቅዠታዊ ሰላማዊ ሰልፍ የሚያደርጉትን በተምለከተ ። የሀገራችንን ታሪክ ለማፋለስ እትዮጵያ እና ኢትዮጵያነት ማለት ውስጠ ሚስጥሩን በቅጡ ሳያጤኑ እንዲሁም ሀገራችንን ለመሸጥ በህልማችው ሆነ በህውናችው አምናም ሲያያቃመጡ ዘድሮም ሲዶሉቱ የከረሙትን እንደ ቢቢሲ (BBC) ፤ የአሜሪካው ድምጽ (VOA) ና መሰል ሳይመለከታችው በአገራችን ጉዳይ ላይ ጥልቅ የሚሉትን ድርጅቶች የሳቱትን ቁም ነገር እንዲገነዘቡት ለማድረግ። እንደችርፍግ ጊዜ ጠብቀው ሳይታክታቸው የቃጡን የባጡን ለመቀፈር ብቅ ጥልቅ የሚሉ እራሳችውን የሸጡ እትዮጵያዊን ተብየ የግዲህ ልጅ ወገኖቻችን <አዛኝ ቅቤ አንጓች>> እንዲሉ ሲያላዝኑ ማየቱ ለተመልካቹ እና ለሰሚው የሚዘገንን እና የሚያሳዝን ድርጊቶች እየፈጽሙ ስለሆነ ከዚህ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ እና እንዲጠነቀቁ ወንድማዊ ምክሮችን ለመለገስ በማሰብ የተከተበ ጽሑፍ ነው ።

እኔ በኢትዮጵያዊ ጭዋነት በእንግሊዝ ፓርላማ ፓሪትኩለስ አዳራሽ/Portcullis house/ የታደምኩት እንደማገኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሬ ጉዳይ ላይ ወገኖቹ እና የውጭ ሀገር ተወላጆች እንዲሁም የኢትዮጵያ ወዳጆች የሚሉትን እንዲሁም ምንያህል እንደሚቀረቀሩላት እና እንደሚያስቡላት ለማየትና ለመታዘብ ነበር።

እኛ ኢትዮጵያዊያን ከሁሉ የሚለየን ለሌላ ዜጋ አለማጎብድደዳችን እና ከአምላክ በስተቀር ሌላ አምላኩ አለመሆናችን ነው። በዚህ ስብሰባ ግን የአዞ እንባ አንቢውች እና አስመሳዮች በጾመ ኩዳዴው ለአምላክ መስገድ ትተው ፍርፋሪ ለሚውረውሩላቸው መንበርከካቸው እና ማርገዳቸው አሳፈረኝ። ያኔ መይሳው ካሳ ፤ አጼ ዮሃንስ ፤ እምየ ሚኒሊክ እና ሌሎች ጀግኖች የአሽራ አባቶቻችን ገድለ ስራ በልቤ ና በፊቴ ውል አለብኝ ። በወገን አሳፋሪወች ላይ የለበጣ ሳቅ ሳቁባቸው ። በቦታው የተመለከትኩአቸውን የኢትዮጵያዊነት በረከቱ የራቃቸው እና ጀግኖች የለገሰዋቸውን የኩራት መንፈስ አውልቀው የጣሉት ወንድሞቼ አስደመሙኝ ነገር ግን የእኔን እንድምታ ና አርምሞ የተጋሩኝ በመኖራቸው ተጽናናሁ።

የኢትዮጵያን ታላቅነት የማይፈልጉ መኸገር ወዘ ልውጥ አሽባሪውች እና በወንጀለኝነት ተርታ መዝገብ ሰፍረው ታሪክ የሚፈልጋችውን ወገን አሳፋሪወችን አካቶ የምንወዳትን እና ጀግኖች ደማችውን ያፈሰሱላትን ታላቁዋን ሃገራችንን እንደልሆነ አድርገው በደቦ ብያብጠለጥሉአትም ከእንግሊዛዊዋ እመቤት

ስለታላቅነታችን መበስሩ ህምየ ኢትዮጵያን ቃና ና ለዛዋን ያጣጣማት እና ማንናትዋን የምያውቃት ያውቃታል ብየ ተሰነይኩ።

ከሁሉ ግን የሚያሳዝነው ኢትዮጵያን በካርታ እንጂ እንደሳት የሚፋጅ ጀግኖች ልጆች ሀገር መሆንዋን ያልትገነዘቡ በቂም እና በተንኮል ሽንፍላችው የተቀዘረ በትላንት ብቻ እንጂ ዛሬን ለመኖር ያልታደሉ (Those who are still living in the past) እንደዚህ በማለት ታሪክዋን አጎደፉ ። <<ወይኔ ሀገሬ በሆን ነበር የልክ የልካቸው ይነገራቸው ነበር>> አልኩ ፤ አዘንኩላችው።

ኦበንጎ ማቶ (ለኔ እኒህ ሰውየ ባዶው ማቶ) ናችው ። የታላቁን ኢትዮጵያዊ የጋምቤላን ሕዝብ ካባ ለብሰው የእንግሊዘኛ ተናጋሪ ሊቅ ነኝ ለማለት ሲሉ እንዲህ በማለት በሃገራችን ታሪክ ተቃለድ፤ ተሳለቁ እንደህም ብለው ዘባረቁ ፤

ፈረንጆች “ sleep of the tongue “ ይሉታል እኛ ኢትዮጵያዊያን ደግሞ ዛያዊ አጋላለጽ አለን እና “እራስ ሲመለጥ እና አፍ ሲያመልጥ አይታወቅም>> እንዲሉ እንዲህ ሲሉ ገለፈጡ በታሪክ ተጠያቂ የሚያደርጋችውን “አላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቅልቃል” ይሉ ዘንድ የሚከተለዉን የሌለ ታሪክ አነበነቡ ፤

“Ethiopian government opposes the black”

“ In Ethiopian history a party never lead by women”

ይህ አባባላቸው በጥሬው ሲተረጎም << የኢትዮጵያ መንግስት ጥቁር ሕዝብ ይቃወማል>> እንዲሁም <በኢትዮጵያ ታሪክ ሴቶች ለፓርቲ መሪነት በቅተው አያውቁም>> በማለት ያልሆነ እራሳቸው የፈጠሩትን ቅዥበተ ታሪክ አነበነቡ ።

የስብሰባዉን አላማ ስቶ መናገር ከስብሳባው መሪ አሳበ ጎባጣ አቃም እና በአገራችን ጉዳይ ላይ እንደ እርጎ ዝንብ ጥልቅ ማለት ልምዳቸው የሆነው ድሮዉንም <ለማያውቁሽ ታጠኝ እኛስ እንተዋወቃለን> ይሉ ዘንድ ያለፈ ስህተት ካለ እንዳይከሰት ከማድረግ ይልቅ በሃገራችን የሽረቡት መተላልቅ ና መናቆር እንዲያገረሽ የተቻላቸውን ለማድረግ ሞከሩ።

ወ/ሮ አና ጎሜዝ ፡ <እነ ጎምዛዜ> ቢባሉ ከሚሻላቸው በድሮ በሬ እስካሁን እያረሱ ያሉትን በመከተል <ጌታዋን የተማመነች በግ ላትዋን ውጭ አሳደረች> ይሉ ዘንድ ፤ በአስተሳሰባቸው እንጭጭ የሆኑ እና እነሱነታቸው ፤ ማንነታቸው የተጭበረበረባቸው ኢትዮጵያዊ ወገን ተብየውች ከኒህ ሴትዮ ጋር በመተባበር በደቦ በታላቅዋ ሀገራችን ላይ ልሃጫችውን እንደአበደ ዉሻ አዝረበረቡ ዋ! ዋ! በባለታሪክ እና ባለአሻራ በሆነችው ኢትዮጵያ ለመቀለድ ሞከሩ ፤ተገተረተሩ፤ አይገባም !!!

አቶ ኦባንጎ ማቶ <<ኢትዮጵያ ጥቁሮችን ትቃወማለች>> ላሉት ኢትዮጵያ ለጥቁሮች ነጻነት አሻራ የጣለች ከመሆንዋ ባሻገር ጥቁር አፍሪካዊያን፤ ካረቢያውያን እና የዘመኑ ስሉጡን አሜሪካዊያን እና መላው አለም እንዲሁም ታላላቅ የአለም መሪወች እነኑኩርማ፤ እነ ማንዴላ ፤ ማርቲን ሉተር ኪንግ እንዲሁም ታላቁ የኢትዮጵያ ወዳጅ ቦምባአርሊ ቢሰሙ አይንህን ላፋር ባሉአቸው እና ባዘኑ ነበር።

ከሁሉ ግን የስብሰባው ተሳታፊ ወገኖቻችን ለስልጣን ከመሽቀዳደም እና የሌለን ነገር በምነአብ እያለሙ ከሞባረቅ ይልቅ ለሀገራቸው ተቆርቁረው የኒህን ሴትዮ ና የአቶ ኦባንጎን ወለም ያልውን ምላሳቸውን በመልካም ምላሽ ባሹላችው ነበር። እኔ ግን ስብሰባዉን ጥየ ወጣሁ። ሀይኔ እንባ እያቀረረ ና ያገሬን የሀዘን እንጉርጉሮ እንዲህ ብየ በመቀኝት ፡

< አወይ አንች ሀገሬ ጀሮሽ ብዙ ሰማ
እንደቀላል እቃ ዉልታሽ ተረሳ ፤

እነአብዲሳጋ እነዘርአይ ድረስ
ጎራው እትንኩብን ኢትዮጵያን ባሉበት ፤

በውጭ ምድር ዛሬ ታሪክ ሽቀጥ ሆነ
እንደመናኛ ህቃ ስምሽ ተሸቀጠ ፤

አብረውም አደሙ
በደቦ አሸረቡ

ክፋሽን ተመኙ
ለጠላት፤ ለክፉ በጣሙን አደሉ

ወደቁ ፤ አረገዱ
እናትነትሽን ንቀው
ጥቅም ይቅደም አሉ

ዘመኖቾቹ የነጭ ጅራቶች
አርምሞን መራጨች

አብረው ቀለዱብሽ
በክፉም አነሱሽ> ዘይገርም ነገር።

ሌላዉ የታዘብኩት ድፍረት ና የአህምሮ ቅኽበት ደግሞ አቶ ኦቦንጎ ማቶ የቅርብ እና የሩቅ የኢትዮጵያዉያን ሴቶች ተጋድሎን እና አመራር ዚቅ በማግባት ተሳለቁ ። <<በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የሴት የፓርቲ መሪውች ተፈጥረው አያውቁም ፤

አልታዩም አሉ>>። <ጆሮ አይሰማው የለ > እንዲሉ ድፍረታቸው ከታሪክ አለማወቅ የመነጨ መሆኑን ታዝቤ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንዳይሳሳት ይሄን መጣጥፍ ልከትብ ተገደድኩ። ይሄን ታሪክ ያላጣቀሰ አባባላቸውን እነ እትጌ ጣይቱ ፡ ማርታ እና መሰል ጀግኖች ሴቶች እህቶቻችን ቢሰሙ ሀይናቸው ላይ ለጠላት የደቀሱትን ድልህ እና ሚጥሚጣ ለድፈው ማንነታችውን ባሳይዋችው ነበር አልኩ ።

ምርጫውን በተመለከተ ያላችውን ቀና አስተሳሰብ መናገር ትተው መዘባረቅ እና ሃገራችንን ከማይግባ ቦታ ፤ በበአድ ቓንቓ ፤ የኢትዮጵያ ታላቅነት በማይዋጥላቸው ፤ ሰላምዋን በማይፈልጉ እስሰቶች ፤ ውብ ማንነትዋ በሚያስቀናችው ፤ ላለፉት ዘመናት ዉጣ ዉረዶች ምክንያት በሆኑ ድራሽ ቢስ የሰው ሃገር ሰውች ፊት ታላቁዋን ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያዊያንን እንደቀላል ነገር መዳፈሩ እንዳይደገም እያሳሰብን በታሪክም ነገ ያሚያስጠይቅ መሆኑን መገንዘብ ግድ ይልዋል።

ከሁሉ ሁሉ ዛሬ በሀገራችን አንጻራዊ ሰላም ሰፍኖ ፤ ተጨባጭ እድገት እንዲሁም ሁሉን ብሔር ብሔረሰቦች ያቀፈ አወቃቅር ተንሰራፍቶ እንዳለ የሚታወቅና የአለም መገናኛ ብዙሃን ሳይቀር ይህንን ተጨባጭ እምርታ እየዘገቡ ያሉበት ውቅት መሆኑ ይታወቃል። ይህ የተመቻቸ የእድገት ፈር እንዲሳለጥ እንዴት አእምሮአችንና መዋለ ንዋያችንን አፍስሰን ሀገራችን እንጥቀም ማለት ሲገባቸው <<እኛ ከሞትን ሰርዶ አይብቃል>> ባዮች አሁንም አሻጥራቸውን እና ደባቸውን አላቆሙም።

እነዚህ ተቃዋሚ ነን ባዮች በዉስጣቸው ያቀፉአችው ጂራቶቻችው የአንድ ስረአት ውጤቶች ፡ ያረጁ ና ያፈጁ ኢትዮጵያን እስከድዳችን ካልበላን የሚሉ አጋሰሶች መሆናቸው ለማንም ግልጽ ነው። መላውን የኢትዮጵያ ብሔር ቤሔረሰቦች በአባልነት ሳያቅፉ ትላንትም እነሱ ዛሬም እነሱ ሆነው እንዳረጀ ከበሮ ሲጮሁ ላያቸው ሊታዘንላቸው የሚገባ ሲሆን ከእድሚያችው መግፋት አንጻር አስታራቂ ቢሆኑ የሚያምርባቸው እና ጊዜ ሳይመሽባቸው ፤ እንዳማረባችው የሰላሙን ትግል ለተተኪው ትውልድ አስረክበው ቢያልፉ የሚሻል መሆኑ ልንነገራቸው ያሚጋባ ይሆናል ።

እነዚህ የትውልድ ነቀዞች በየድህረ ገጹ፤በየስብሰባ ቦታው እና በየመሸታ ቤቱ ሁሉ <በሬ ወለደ ፣ አዛኝ ቅቤ አንጓች፤ የሌለ ወሬ አናፋሽ > ግልገል ጊቤ ፡ ተከዜ እና መሰል እሰየው የምያስኘ እድገቶች ታዩ ከሚሉአቸው ይልቅ በዚህ የኢትዮጵያ አካባቢ ጦርነት ተነሰቶ ይህን ያህል ሰው ሞተ ብሎ ዉሸት/Fantasy; Fairytale/ ወሬ ቢያወሩላቸው የሚያሰንያቸው ናቸው።

የኢትዮጵያ ሕዝብ መተላለቁን የሚመኙ ፤ የኢትዮጵያን እና የሕዝቦችዋን ክፉ ሲሰሙ < አሸሸው ገዳሜ > ሲሉ ማምሸት የሚቀናቸዉን እና ከጠላት ጋር ተሰልፈው ያጎረሰቻቸውን እና የቀለም መቃ ያስጨበጠቻቸውን እምየ ኢትዮጵያን

ሊወጉ የተነሱ ስለመሆኑ እና በዚህም አካሄዳቸው የህፍረት ካባ እየተላበሱ ያሉ ስለመሆኑ መናገር ለቀባሪ እንደማስረዳት ነው።

እነዚህ የታሪክ ተጠያቂወች ትላንት በስልጣን በነበሩበት ጊዜ ብሔር ብሔረሰቦችን ዞር ብለው ሳያዮ በውጭ ሃገር ተጎልተው የብሔር ብሔረሰቦች ተቆርቋሪ መስለው መቅረባቸው <ሆድ ሲያውቅ ደሮ ማታ>> ልንላቸው ይጋባል።

ብሔር ብሔረሰቦች አካባቢ ግድብ ተሰርቶ ና የመሰረተ ልማት እንቅስቃሴ ተጀምሮ ህይወታቸው እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ህብረተሰብ አካል ኑሩዋቸው እንዲለውጥ እንቅስቃሴ ሲጀመር ስራው እንዲሳለጥ የተቻላቸውን ከማድረግ ይልቅ እኛን ሊቆቹን ሳያነጋግሩ ቀርተው አገር ፈረሰ ፤ ጎርፍ ወሰዳቸው ብለው የሚያወሩ ናቸው። በቱርማ ኦሞ ወንዝ ና በሌሎች አካባቢወች የሚኖረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ኣካል በየአካባቢው መኖሩን ትላንት የስልጣኑን ልሻእም እንደሻቸው ሲስቡት በነበረት ወቅት ማውቅ አልመቻላቸውን ዞር ብለው ማየት ተስኑአችው ና ይህን አለማድረጋችው ሳይቆረቁራቸው ደርሶ እነ ኢንጂነር እና እነ ዶክተር እኛ እናውቅላችዋለን ሲሉ ድፍረታቸው የለበጣ መሆኑ ለማንም ግልጽ ነው ።

የአዲስ አበባ ዮኒቭርሲቲ እና የኢትዮጵያ እውቅ ተቃማት አንሽራቶ የገፈተራችው ጥርቅሞች የአለአግባብ በሚያገኙት የውጭ መንግስት የይስሙላ ቻሪቲ / መንግስት በቀል ያልሆነ/ የህርዳታ ገንዘብ ሆዳቸዉን በምናምኑ እና በሚውጡት ነገር ተጎጥሮ ድለሉ ተጠራቅሞ የቱርማን ሕዝብ ያፈናቅለዋል ፡ ከእርሻው ያስተጉአጉለዋል ፡ ያልሆነ መጥፎ ህልማቸዉ እና ቅዠታቸውን <survival international እና የሀገር ልጅ> << መልከ ጥፉን በስም ይደግፉ>> ይሉ ዘንድ እንደነዚህ ካሉ ተለጣፊ ቅን ከማያስብ ድርጅት ጋር እንደ ጥገኛ በመሆን መስበካቸው ኢትዮጵያዊነታችው ዉጭ ሀገር ብዙ ከመቆየት የተነሳ ተዘንግቶአቸው በሚረዱቸው አካላት ጭንቅላት እያሰቡ ስለመሆኑ ለመናገር ከሚቻልበት ወቅት ተደርሰዋል።

የሚጽፉት ጽሁፍ እና የሚደሰኩርት ያልተጨበጠ ወሬ እና የማያልቅ የገደል ማሚቶ ጩህታችው እራሳችው በፈጠሩት ድህረ ገጹ እና በየመሸታ ቤቱ ብርጭቆ ላይ በሚያስቀይም ሁኔታ ሰፍሮ ሰላለ እማኝነቱን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ መተው በቂ ይሆናል ።

ከዚህ አልፎ የኢትዮጵያና የሕዝቦችዋ ነጻነት በንዋይ የማይለወጥ አስፍላጊው የሕይወት መስዋትነት ተከፍሎ ለዘላለም ተከብሮ የኖረ እና የሚኖር መሆኑ እንደ ቢቢሲ / BBC / የአሜሪካው ድምጽ / VOA / እና ለሌሎቹ እኛነታችን ላላወቁ አሽባሪወች ሊነግራቸው የሚገባ ይሆናል። ከዛሬ ሃያ አምስት አመት በፊት እና ቀደም ብሎ ለተፈጠሩት ድርቆች እና ችግሮች ተጠያቂውቹ የስረአቱ መሪወች እንዲሁም ተፈጥሮ ሊሆን የሚችል ነው ። በዝህ ወቅት ላይቭ ሄድ

/ LIVE AID / በአለም አቀፍ ደረጃ በግልጽ እና በተደራጀ መልኩ ተደርጎ የተዋጣው ገንዘብ ለነጻ አውጭውች መሳርያ መግዣ ውልዋል ብሎ በምርጫ ወቅት ማውራቱ ወገንን ከወገን እና ዘርን ከዘር ለማፋጀት እንጂ ለኛ ለኢትዮጵያውያን አስበው ነው ብሎ የሚያስብ ወገን ካለ << ለትልቅ እና ለአዋቂ ሰው ወተት በጡጦ >> ለመስጠት እንደማሰብ የሚያስቆጥር ነው። ይህ መሰሉ የጋዜጠኘነትን ምያዊ ግዴታን /Ethics / ያልጠበቀ፤ የግዴለሽነት እና የዘፈቀደ ጣልቃ ገብነት ሊነቀፍ የሚገባ ይሆናል ። ከነዚህ ቡድኖች ጋር የሚያጨበጭቡ ወገኖች ካሉ ኢትዮጵያን እና እራሳቸውን ማወቅ የተሳናቸው መሆኑ ሊነገራቸው የሚገባ እንዲሁም በነጻነቱና በሃገሩ የሚቀልድ ዜጋ <<የአዋቂ አጥፊ>> የሚያሰኘው እና በታሪክ ተጠየቂ እንደሚያስደርግ ሊታወቅ ይገባል።

እንዲያው ውሸት ሲበዛ እንዳዴም ዝም ማለቱ ያልታወቀባቸው የመሰላቸዋል በሚል እንደዝህ ያሉ ጽሁፎችን በመጻፍ ማጋለጡ ይጋባል በማለት እንጂ ትላትናም ሞክረው ስላልተሳካላችው <ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም> እንዲሉ ያምናውን መፈክራችውን ይዘው ስለተነሱ እና መላው የኢትዮጵያም ሕዝብ ሰላወቃቸው የትም እንደማይደርሱ ከአጀማመራቸው ማወቅ ይቻላል። ያን ያህል ለነዝህ መሰሉ የታሪክ አተላወች እና በሕዝብ ደም በቀለዱ የታሪክ ተጠያቂውች ላይ ፍርዱን ለታላቁ እግዚአብሔር እና ሕግ እስኪጠይቃቸው ያለያም በደላቸው ጸጽቶአቸው ወገናቸውን ይቅርታ እስኪጠይቁ ድረስ እድሉን መስጠት የጋባል በማለት ልናስረዳቸው እና <እኛም አውቀናል ጉድጉአድ ምሰናል>> ልንላቸው ይጋባል በማለት ማስረግጥ የሚጋባ ይሆናል።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ልያውቁት ፡ ሊገነዘቡት እና በአእምሮዋቸው ሁልጊዜም ሊያጤኑት የሚገባ ነገር ቢኖር የአንድ ሀገር ህዝቦች በሚስማሙባቸው ጉዳዮች ላይ በጋራ ተባብረው ለኢኮኖሚ እድገት፤ ለማህበራዊ ሕይወቶች መሳካት ና ለልማት መስፋፋት መነሳሳታቸው ከማንኛውም የበለጠ ሊተኮርበት የሚገባ ጉዳይ ሲሆን ይህ የሀገር እሴት ለሁላችን ታላቅ ተስፋ ሰጪ እና ቸል የማይባል ጉዳይ ነው። ይህን ለመከወን አእምሮአችንን ከተለያዮ አስሮ ሊገድቡን ከሚችሉ ጥቃቅን ስንኮች በመራቅ ልንቀሳቀስ እና ልንገፋበት ግድ የሚለን ሲሆን የግል ፍላጎት ሲሳካ ክልብ የሚያስፈነድቀው ሀገራችን አድጋ ምድራችን የሁላችን መናህሪያ እና ያማረች ምድር ሁና ስናያት ብቻ ነው ::

ይህን አምለካከት እና ጽንሰ ሃሳብ አበው አባቶቻችን እና የአለም ታላላቅ ሰወች ሲያስተጋቡት የነበር ከመሆኑ ባሻገር ሕይወታችውን የሰውለት አያሌ መሆናቸውን ልንገነዘብ የግድ የሚለን ይሆናል። ሀገር ክፉ ሲያጋጥማት ሆ ብሎ መነሳት የሁሉም በተለይ የኛ ኢትዮጵያዊያን እንደ ባንዲራችን መገልጫችን መሆኑ የቅርብ ጊዜ ትዝታ እና የውረስነው ቅርሰ ሀብታችን ነው ::

ነገር ግን አባቶቻችን እንደወርቅ በነጠረ አባባላቸው ሰላም በተንሰራፋበት ወቅት ‘’ድር ቢያብር አንበሳ ያስር’’ ማለታቸው ሀይለኛውን ችግር ለማንበርክርክ ሳይለያዮ በጋራ ሀብታሙ፣ቀለም የቀጠረው፣ ስራተኛው፣ ገበሬው እና መላ ሕዝቡ በአንድ ይረባረብ እንደነበር ማንሰላሰሉ የግድ እንዲለን የተቀኙልን ምሳሌያዊ አነጋግር መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል::

ከዚህ በመነሳት መላው የኢትዮጵያ ህዝብ ውጭ ሀገር ያለውም ሆነ ሀገር ውስጥ ያለው ምድራችን ስትድፈር እምቢ ለህግሬ ብሎ በጋራ እንድሚነሳ ሁሉ እምቢ ለድህነት በማለት አሁን ያለውን አንጻራዊ ሰላም በመጠቀም አንድ በሚያደረጉን ጉዳዮች ላይ ተሰባስቦ እና ተደራጅቶ መጪውን የኢትዮጵያ ህዳሴ ለማጎልበት ና ለማጠናክር መነሳሳቱ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ የወቅቱ ጥያቄ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል። ታሪክ እንደሚያሳየን መንግስታት ያልፋሉ ፣ ሰው የተፈጥሮ ግዴታ ነውና ያልፋል ነገር ግን የማያልፍ ነገር ለተተኪው ትውልድ እንደ አባቶታችን ልዩነታችን በማቻቻል ተሰፋ የሚሰጥ ሀውልት ተክሎ ለማለፍ በጋራ መነሳሳቱ የአሁኑ ትውልድ እና ሀገሩን የሚውድ ሁሉ ጸሀይ ሳትጠልቅ ሊያስብበት የሚገባ ጉዳይ ነው ::

ማንኛውም የሕይውት ጉዞ ሆነ ሳይንሳዊ የምርምር ሂደት እንዳሳየን እና እንዳስተማረን የሕዝብን ስሜት፤የጋራ አስተሳሰብ፤ጥቅም እና ፍላጎት አዛምደው ና አቀራኝተው ሳይንሱ እንዲሁም ሳይታጠቁ በግል ራሀይ ሆነ በፖለቲካ መነባንብ ግዝፈት በመጥመዝምዝ መባክኑ የራስን ፍላጎት እና አስተሳሰብ እንደማራምድ ይቆጠራል እንጅ የሀገሬውን የጋራ የታሪክ ግኝት ጥቅም እና ፍላጎት አፋፍ እንድማያድርሰው የታየ እና ከሌሎች ካደጉ ሀገሮች ያይነውና እያየነው ያለ ጭብጥ ነው። ከዚህ ወጣ በለው የሀገርን ጥቅም እና የጋራ አስተሳሰብ ስንቅው እንዲሁም የፖለቲካ ሆነ የግል ራሀያቸውን እያዛመዱ የተንቀሳቀሱት ቡዱኖች አንቱ የተባሉ ሰራውች እንደሰሩ ልንግነዘብ እና ይህን መካድ ግን አይንን በጨው እንድማጠብ የሚያስቀጥር ይሆናል:: ይህን ጽንሰ ሀሳብ ተንትርሶ የአለም ታላላቅ ሰወችም እንደኛውቹ አያቶችችን እንዲህ ብልው ከትበውታል፤’’Thus to be independent of public opinion is the first formal condition of achieving any thing great or rational life, or science. Great achievement is assured, how ever, of subsequent recognition and grateful acceptance by public opinion, which in due course will make it one of its own” Heiniric Heine, 1797-1856”

ከዚህ በተጨማሪ የመጻህፍቶች ሁሉ ቁንጮ የሆነው መጽሀፍ ቅዱስ ሆነ ቁረአን መልካም ነገር ስለማድረግ እንዲህ በማለት ሀትቶአል ‘’ be carful to devote themselves all men to what is good. These things are excellent and profitable for every one’’ይህም ማለት መልካም ማድርግ እና ሌሎችን ወደ መልካም መንገድ መምራት ትርፋ ከትርፎቹ ሁሉ የላቀ መሆኑን እያስተማረን ሲሆን ለሀገር ብሔራዊ ጥቅም ሆነ ድህንነት ለጋራ ጉዳይ

በጋራ መረባረብ በማንኛውም መልኩ ቢሆን እሰየው የሚያሰኝ እንደሆነ እያስተማረንም ነው::

እንዲሁም የጥቂት ሰውችን ሆነ በተለያየ ስም ተደራጂተው የሚንቀሳቅሱ ቡድኖችን ፍላጎት እና ሕልም ብቻ እያሰቡ እና እያራምዱ በአላማ መለያየት ዙሪያ አትኩሮ የሀገርን የጋራ ጉዳይ ወደጎን ትቶ መወዛወዙ አዳጋች እና የትም እንደምያደርስ ተቀምጡአል፡፤ “ A little group of will full men representing no opinion but their own; have rendered the countries helpless and contemptible ‘The New York Times.

ከዚህ በመነሳት መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በኛ በኩል ደግሞ በውጭ ሃገር ያለነው ኑዋሪውች የተለያየ የአላማ፤ የፖለቲካ እና የአመለካከት ልዩነት ቢኖረንም ከቀምንለት አላማ ጎን ለጎን ለሀገራችን ሕዝቦች የጋራ ጥቅም ፡ ልማት እና እድገት በደቦ ልንረባረብ የግድ የሚለን መሆኑን የተቀመጠ ሲሆን በዚህ መልኩ ቀና አመለካከት ይዞ በጋራ መንቀሳቀሱ የታላቅነት መለኪያ መሆኑን እንዲህ ብለው ታላቁ ፈላስፋ አስቀምጠውታል “A constitutional states man in general a man of common opinion and uncommon abilities” Sir Robert peel::

እኛ ኢትዮጵያውያን በተለይ ውጭ ሀገር ንዋሪ የሆነው ሰላማችን እና ድንበራችን በሌላ የውጭ ሀገሮች ተነክቶ የቅርና በክፉ ያነሳትን ሳይቀር በጋራ ማፋጠጥና የምንከራክርላት መሆኑን መናገር ለቀባሪ እንደምርዳት ነው። ነገር ግን አንጻራዊ ሰላም በሰፈነ ወቅት በትንሽ ስንክ መፋተጉን ና መንታረኩን ወደጎን ትተን እንዲሁም በፖለቲካ አላማ ትልቅነት እና ጥልቀት መወዳደሩን ለሕዝብ ዉሳኔ ሰጥተን በጋራ በሚያገናኙን ጉዳዮች ላይ ነገ ጋብቻ ስናስብ የምንዳርባት ፤ ሲከፋን የምንሸሸግባት ታሪክ ያላት የተስፋ ምድራችን ስለሆነች ለምንወዳት ሀገራችን የታሪክ አሻራ ጥለን ስጋችን ሰላም አግኝታ የምታርፍባት ምድር ትሆን ዘንድ በጋራ ልንረባረብላት ይገባል። ይህንንም የተቀደሰ ሃሳብ “የዝብሪት ቤት ሳየዘጋ ያድራል” የሚለው ደርሶብን ጠላት እንዳይገባብን እንዲሁም የሚከተለውን የእንግሊዘኛ መጣጥፍ አንግበን በጋራ ሊንቀሳቀስበት እንደሚገባ በሚከተለው መልኩ ተጠቅሶልናል “ our researcher into public opinion are content that held the proper opinions for the time of year; when there was peace ,he was for peace ,when there was war ,he went” 1940 ይህን አምለካክት በኛ ታሪክም እንደ አጼቴውድሮስ፡ አጤሚኒሊክ ፤አጤ ዮሐንስ እና መሰል በሳል መሪወቻችን በጋራ ሰሩ ፣ ችግር ሲፈጠር በአንድነት ተነሱ በማለት የአንድነትን ጠቃሚታን አስምርውብት ያለፉ ሲሆን የአሁኖቹ የተለያዩ የአገራችን የፖለቲካ ፓርቲውች ሆነ መሪወች አንድ በሚያድርጉን ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሰጥተን የሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ከፍትጊያ የነጻ ይሆነ አህጉር እና ሀገር የመፍጠር ጭብጥ አለማቀፋዊ አላማ /Globalization/አንግበን ልዩነቶቻቸውን በማማቻል በጋራ ልንቀሳቀስ፤ ልንገፋበት እና ሁላችን ልንነሳሳበት ይገባል ::

ይህን በማለት የተሰፋ እና ህትብታችን የተቀበረባትን የታላቁዋን ኢትዮጵያን ሰላም ፤ እድገትና አሻራ ጠብቀን እና ተቀራርበን በመካከላችን ተቆርቋሪ መስለው ልያናኩሩን እና ሊያዳሙን የሚነሱ አይሎችን በማውገዝ ለመጭው ትውልድ የአደራ አሻራ እንደአባቶቻችን ጥለን ለማለፍ የሁላችን መሻት ና መነሳሳት እንዲሆን በማለት መጣጥፉአን ለዛሬው በዚህ እደመድማልሁ።

ኢትዮጵያ ሃጋራችን የምንኮራባት ወደር የለሽ ምድር ናት
በጋራ እናልማት ፤ እንጠብቃት ።

እዉነት መዝገቡ / ከምድረ እንግሊዝ/